የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ---/2008 ዓ.ም.

## <u>ሀላይደጌ አሰቦት ብሔራዊ ፓርክን ለመሰየም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 አንቀጽ 4(2) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "ሀላይደጌ አሰቦት ብሔራዊ ፓርክን መሰየሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ------/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

1/ "አዋጅ" ማለት የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 ነው፤

2/ በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

3/ "ጉልት" ማለት ከጠንካራ ነገሮች ተሠርቶ የትሪጎኖሜትሪክ ነጥቦች የቅየሳ ዘዴ በድንበር ላይ የሚተከል ቋሚ የቅየሳ ምልክት ነው፤

4/ "ባለስልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር 575/2000 የተቋቋመው የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤

5/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

6/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>ሀላይደጌ አሰቦት ብሔራዊ ፓርክ መሰየም</u>

በአዋጁ አንቀጽ 4 መሠረት "ሀላይደጌ አሰቦት ብሔራዊ ፓርክ" (ከዚህ በኋላ "ፓርክ" እየተባለ የሚጠራ) በፌዴራል መንግስት የሚተዳደር ሆኖ በዚህ ደንብ ተሰይሟል፡፡

4. <u>የፓርኩ ዳር ድንበር</u>

ፓርኩ በአፋር እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልሎች ውስጥ 1099.23 ካሬ ኪ.ሜ የቆዳ ስፋት የሚሸፍን ሆኖ በሚከተሉት አዋሳኝ ስፍራዎች ውስጥ ይገኛል::

1/ ምእራብ ሀረርጌ ዞን ሚኤሶ ወረዳ ደንበ ሁነዴ ሚሶማ ቀበሌ ልዩ ስሙ ደባደሊ ላይ በ 09 ዲግሪ 15 ደቂቃ 10 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 39 ደቂቃ 16 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ ከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር 1 በመነሳት፤

2/ ከዚያም ተመሳሳይ አቅጣጫን ተከትሎ ልዩ ስሙ ቂሌ ለሚ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 15 ደቂቃ 11 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 37 ደቂቃ 34 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር 2፤

3/ ከዚያም በተመሳሳይ አቅጣጫ ልዩ ስሙ ወለሸዋ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 15 ደቂቃ 28 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 35 ደቂቃ 51 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 3፤

4/ ከዚያም ተመሳሳይ አቅጣጫን ተከትሎ ጭሬሳ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 15 ደቂቃ 35 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 35 ደቂቃ 40 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 4፤

5/ ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ ጨሬቻ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 15 ደቂቃ 44 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 35 ደቂቃ 35 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 5፤

6/ ከዚያም ተመሳሳይ አቅጣጫን ተከትሎ ልዩ ስሙ ጠደቻ በልዩ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 15 ደቂቃ 13 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 35 ደቂቃ 21 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 6፤

7/ ከዚያም ወደ ደበብ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ልዩ ስሙ ቆቆይ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 15 ደቂቃ 2 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 35 ደቂቃ 9 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 7፤

8/ ከዚያም ተመመሳይ አቅጣጫን ተከትሎ ልዩ ስሙ ቆቆሮ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 14 ደቂቃ 53 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 35 ደቂቃ 4 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 8፤

9/ ከዚያም በተመሳሳይ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ልዩ ስሙ ለገ ሜይጢ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 14 ደቂቃ 47 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 34 ደቂቃ 37 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 9፤

10/ ከዚያም ተመሳሳይ አቅጣጫን ተከትሎ ልዩ ስሙ ሃብሮ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 14 ደቂቃ 43 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 34 ደቂቃ 22 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 10፤

11/ ከዚያም ተመሳሳይ አቅጣጫን ተከትሎ ልዩ ስሙ ብዮ ደዶታ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 14 ደቂቃ 31 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 34 ደቂቃ 13 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 11፤

12/ ከዚያም ተመሳሳይ አቅጣጫን ተከትሎ ልዩ ስሙ ዱይዳ ኡታሎ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 13 ደቂቃ 53 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 33 ደቂቃ 15 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተዉ ጉልት ቁጥር 12፤

13/ ከዚያም በተመሳሳይ አቅጣጫ ልዩ ስሙ ወልዳ ዲሞቱ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 11 ደቂቃ 11 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 30 ደቂቃ 7 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተዉ ጉልት ቁጥር 13፤

14/ ከዚያም ተመሳሳይ አቅጣጫን ተከትሎ ልዩ ስሙ ሳላቃላ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 10 ደቂቃ 21 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 29 ደቂቃ 41 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 14፤

15/ ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ልዩ ስሙ ሳላዳባ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 10 ደቂቃ 36 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 27 ደቂቃ 10 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 15፤

16/ ከዚያም የደቡብ ምዕራብ አቅጣጫን ተከትሎ ልዩ ስሙ ጕባ ሀጣዊ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 8 ደቂቃ 47 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 24 ደቂቃ 6 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 16፤

17/ ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ ልዩ ስሙ ቡሬ አርባ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 3 ደቂቃ 41 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 22 ደቂቃ 14 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር 17፤

18/ ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ በአፋር ክልል ገቢረሱ ዞን አሚባራ ወረዳ ሀላይደጌ ቀበሌ የሚገኘውን ልዩ ስሙ ላያጊሊ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 3 ደቂቃ 53 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 21 ደቂቃ 37 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 18፤

19/ ከዚያም የሰሜን ምዕራብ አቅጣጫን ተከትሎ ልዩ ስሙ ቡሬ አርባ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 5 ደቂቃ 2 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 21 ደቂቃ 13 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 19፤

20/ ከዚያም ወደ ደበቡ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ልዩ ስሙ ቡሬ አርባ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 3 ደቂቃ 53 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 18 ደቂቃ 54 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 20፤

21/ ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመታጠፍ ልዩ ስሙ ረመሳ /መከላከያ ካምኘ/ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 10 ደቂቃ 27 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 21 ደቂቃ 47 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 21፤

22/ ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ልዩ ስሙ ያሎ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 11 ደቂቃ 12 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 19 ደቂቃ 1 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 22፤

23/ ከዚያም የደበብ ምዕራብ አቅጣጫን ተከትሎ ልዩ ስሙ ሱኩራ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 10 ደቂቃ 45 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 17 ደቂቃ 32 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 23፤

24/ ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ልዩ ስሙ ተሰኩቲ-ሃራ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 17 ደቂቃ 34 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 22 ደቂቃ 28 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 24፤

25/ ከዚያም የሰሜን አቅጣጫን ተከትሎ ልዩ ስሙ ደቢደሊ /ካምኘ ሣይት/ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 18 ደቂቃ 49 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 22 ደቂቃ 29 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 25፤

26/ ከዚያም የሰሜን ምዕራብ አቅጣጫን ተከትሎ ልዩ ስሙ .........በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 20 ደቂቃ 44 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 21 ደቂቃ 57 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 26፤

27/ ከዚያም ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ልዩ ስሙ አማደዱ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 20 ደቂቃ 42 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 22 ደቂቃ 17 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 27፤

28/ ከዚያም የሰሜን ምስራቅ አቅጣጫን ተከትሎ ልዩ ስሙ መርዲርተሌ አዳዲ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 21 ደቂቃ 54 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 23 ደቂቃ 41 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 28፤

29/ ከዚያም የሰሜን አቅጣጫን ተከትሎ ልዩ ስሙ ቢደርደራ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 26 ደቂቃ 27 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 25 ደቂቃ 26 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 29፤

30/ ከዚያም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ልዩ ስሙ ቴሌ /አስፋልት/ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 28 ደቂቃ 40 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 22 ደቂቃ 50 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 30፤

31/ ከዚያም የሰሜን አቅጣጫን ተከትሎ ልዩ ስሙ ረመሳ /መከላከያ ካምኘ/ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 29 ደቂቃ 46 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 22 ደቂቃ 50 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 31፤

32/ ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ልዩ ስሙ ዳቴ ገርሳ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 33 ደቂቃ 29 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 26 ደቂቃ 42 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 32፤

33/ ከዚያም ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመጣጠፍ ልዩ ስሙ አይጉ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 33 ደቂቃ 24 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 27 ደቂቃ 22 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 33፤

34/ ከዚያም የስሜን ምዕራብ አቅጣጫን ተከትሎ ልዩ ስሙ በደና በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 36 ደቂቃ 17 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 26 ደቂቃ 15 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 34፤

35/ ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ልዩ ስሙ በደና በተባለ ቦታ ላይ ምሥራቅ በ9 ዲግሪ 38 ደቂቃ 26 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 30 ደቂቃ 52 ሴኮንድ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 35፤

36/ ከዚያም ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ልዩ ስሙ በደኔ በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 36 ደቂቃ 57 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 37 ደቂቃ 60 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 36፤

37/ ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ ልዩ ስሙ በደና በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 29 ደቂቃ 59 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 34 ደቂቃ 32 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 37፤

38/ ከዚያም የምስራቅ አቅጣጫን ተከትሎ ልዩ ስሙ በደና በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 25 ደቂቃ 33 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 27 ደቂቃ 48 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር 38፡፡

39/ ከዚያም ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ልዩ ስሙ በደና በተባለ ቦታ ላይ በ9 ዲግሪ 22 ደቂቃ 24 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 35 ደቂቃ 48 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ የተመለከተው ጉልት ቁጥር 39 ከመነሻው ጉልት ቁጥር 1 ጋር ይገጥማል፡፡

## 5. <u>የፓርኩ አስተዳደር</u>

1/ ባለሥልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 575/2000 አንቀጽ 4 መሠረት በአሚበራ ወረዳ ውስጥ በሚያደራጀው የፓርኩ ጽሕፈት ቤት አማካይነት ፓርኩን ያለማል፣ ያስተዳድራል፣ ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈጸሙበት ይከላከላል፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የፓርኩ አማካሪ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ “ኮሚቴ” እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

## 6. <u>የኮሚቴ አባላት</u>

ኮሚቴው የሚከተሉት አባላቶች ይኖሩታል፤

1) የፓርኩ አዋሳኝ ወረዳዎች ዋና አስተዳዳሪዎች (በየዓመቱ በመቀያየር)…………………………………………………ሰብሳቢ

2) የአሶቦት ገዳም አስተዳዳሪ ………………………………………………አባል

3) የፓርኩ አዋሳኝ ወረዳዎች ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች …………………………………………………..አባላት

4) የፓርኩ አዋሳኝ ወረዳዎች አስተዳደር ኃላፊዎች………………… …..አባላት

5) የፓርኩ አዋሣኝ ወረዳዎች ሀገር ሽማግሌዎች ተወካዮች……………….አባላት

6) የፓርኩ አዋሳኝ ወረዳዎች ሴቶችና ወጣቶች ማህበራት ሁለት ተወካዮች ……………………………………………………አባላት

7) የፓርኩ አዋሳኝ ወረዳዎች የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አንድ ተወካይ……………………………………………………........ አባል

8) የፓርኩ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ……………………………… አባልና ፀሐፊ

## 7. <u>የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባራት</u>

ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1/ የፓርኩ ጽሕፈት ቤት የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት እንዲወጣ ምክር ይሰጣል፤

2/ በፓርኩ አካባቢ የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ባለቤትነት ተሰምቷቸው በፓርኩ አጠባበቅ ላይ የጎላ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ሃሳቦችን ያቀርባል፤

DRAFT

3/ የፓርኩን ጽሕፈት ቤት ዓመታዊ እቅድ እና የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ከመቅረቡ በፊት መርምሮ አስተያየት ይሰጣል፡፡

8. <u>የኮሚቴው ስብሰባ</u>

1/ ኮሚቴው በየሦስት ወሩ አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2/ ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

3/ የኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

9. <u>የተከለከሉ ተግባራት</u>

በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 አንቀጽ 5(1) ከተመለከቱት የተከለከሉ ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉትን ተግባራት በፓርኩ ክልል ውስጥ መፈፀም የተከለከለ ነው፤

1/ መርዛማ ንጥረ ነገሮችን ይዞ ወደ ፓርኩ ውስጥ መግባት፤

2/ ለምግብ መያዣና ለመሳሰሉት የተጠቀሙባቸውን ቆሻሻዎች በዘፈቀደ በየቦታው በፓርኩ ውስጥ መጣል፤

3/ የእንስሳት ማጥመጃ ወይም ማደኛ መሣሪያ ይዞ ወደ ፓርኩ ውስጥ መግባት፡፡

10. በአሰቦት ተራራ ላይ ወደ ሚገኘው ጥንታዊ ገዳም ለሀይማኖታዊ ስነስርአት የሚመጡ ሰዎች ከማናቸውም ክፍያ ነጻ ናቸው፡፡

11. <u>አስተዳደራዊ ቅጣት</u>

DRAFT

1/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 ወይም በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 አንቀጽ 5(1) የተከለከሉትን ተግባራት በመተላለፍ በዱር እንሰሳት ወይም በዱር እንስሳት ሀብት ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት መቀጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 ላይ በተቀመጠው የዋጋ ተመን መሠረት የዱር እንስሳውን ወይም የዱር እንስሳት ሀብቱን ዋጋ ይከፍላል፡፡

2/ ባለሥልጣኑ ፓርኩ ከሚገኝበት አካባቢ አስተዳደር ጋር በመነጋገር ወደ ፓርኩ ክልል የሚገቡ በቤት እንስሳትን በሚመለከት የሚጣል ከአካባቢው ነዋሪዎች አቅም ጋር ተመጣጣኝ የሆነ አስተዳደራዊ መቀጮ ተመን ሊያወጣ ይችላል፡፡

12. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው የፓርኩን ዳር ድንበር ለማስከበር በሚደረገው እንቅስቃሴ ከባለሥልጣኑ ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

13. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ቀን 2008 ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

DRAFT

DRAFT


Hallaydeghe_Assebot National Park
N
Legend
Hallaydeghe-Assebot NP
Hallaydghe_Assebot NP
Area: 1099.23 Sq.km
10 5 0 10 Kilometers
Coordinate System: WGS 1984 UTM Zone 37N
Projection: Transverse Mercator
Datum: WGS 1984
False Easting: 500,000.0000
False Northing: 0.0000
Central Meridian: 39.0000
Scale Factor: 0.9996
Latitude Of Origin: 0.0000
Units: Meter